# በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይ ያንዣበበው የዘር ማጽዳት/ የዘር ማጥፋት አደጋና የእያንዳንዳችን ህላፊነት

ታህሳስ 15፣ 12፣ 2010 (ዲሰምበር 24፣ 2017)

**ከጊዜው ደረሰ**

Gezew.derese@bell.net

## መነሻ

በተለያዩ ሀገሮች የተካሄዱ የዘር ማጥፋት ወይም የዘር ማጽዳት ወንጀሎችን ስንመረምር በተደጋጋሚ ከሚታዩት ልዩ ልዩ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ ይህን አሰቃቂ ወንጀል በጊዜ ለማስቆም ባለመቻላቸው ብዙዎች መጸጸታቸውን ነው። ለዚህ ደግሞ ከሚሰጡት መከንያቶች ውስጥ ስለሁኔታው በጊዜ አለማወቅ፣ የሰው ልጅ የዚህ አይነት ጭካኔ ሊፈጽም ይችላል ብሎ አለማመን፣ አደጋው እንዳይደርስ የማድረጉን ህላፊነት ሌሎች ይወስዳሉ ብሎ መገመት፣ እኔ ምን ልሰራ እችላለሁ ብሎ የራስን ህላፊነት ዝቅ አድርጎ መውሰድ... ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው።

በሩዋንዳ፣ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1994 የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ዘመቻ፣ የሀገሪቱ ፕሬዚደንት በአውሮፕላን አደጋ እንደሞቱ ወዲያውኑ ይጀመር እንጂ፣ ወደዚህ ጥፋት የተደረገው ጎዞ ግን አዝጋሚና በብዙ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች ሲገለጥ የቆየ ነበር።

በሩዋንዳ የዘር ማጥፋቱ ተግባር ሰለባ የሆኑት የቱትሲ ማህበረሰብ አባላት በተለያየ መልክ አድሎና ጥቃት ሲፈጸምባቸው ብዙ አመታት የቆየ ነበር። የሀገሪቱ ዜጎች በብሄር ተለይተው በመታወቂያው ላይ ከየትኛው ብሄር አባል እንደሆነ መግለጽ ግድ ስለነበር፣ ግድያው ሲጀመር ሁትሲዎችን ለመለየት መታወቂያቸውን መመልከቱ ብቻ በቂ ነበር።

የ1994ቱ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ከመጀመሩ ቀደም ባሉት ሶስትና አራት አመታት፣ በሀገሪቱ ባለስልጣኖችና የፖለቲካ መሪዎች አነሳሽነት፣ 16 ያክል ጥቃቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚኖሩ የቱትሲ ማህበረሰብ አባላት ላይ ተፈጽመው ነበር፡፡ በነዚህ ጥቃቶችም በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ ንብረታቸውም ወድሟል፣ ከመኖሪያ ቦታቸው ተፈናቅለዋል። ሆኖም ግን ይህን ጥፋት የፈጸሙ ባለስልጣኖች ይህ ነው የሚባል ቅጣት አልደረሰባቸውም ነበር። አለም አቀፉ ህብረተሰቡም የሚሆነውን ሁሉ በትክክል በበቂ ደረጃ ቢያውቅም ቀጣዩን ጭፍጨፋ ለማስቆም ከመጣር ይልቅ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ማለፉን መርጦ ነበር።

እነዚህ ሁሉ እንዲቆሙ ያልተደረጉ ተግባሮች ተጠናክረውና ሁለንተናዊ መልክ ይዘው በመጨረሻ ከሂትለር እና ሞሶሎኒ የሁለተኛው አለም ጦርነት ጭፍጨፋ ወዲህ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በብዙ ሽህ ለሚቆጠሩ ቱትሲዎች (Tutsi ) ጥፍጭፋ በር ከፋች ሁኔታዎችን አመቻቸ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህወሀት መራሹ መንግስትን እየገጠመው የሚገኘው የውስጥና የውጭ ቀውስ ከጠበቀው በላይ አየተመስቃቀለ፣ የሚይዝ የሚጨብጠውንም እያሳጣው ይገኛል። በመላ የኢትዮጵያ ክፍሎች እየተስፋፋ የመጣው ተቃውሞና አመጽ አገዛዙን እጅግ እያስጨነቀው ነው። ባለፉት ሶስት አመታት በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በኮንሶ ክልሎች ወዘተ የተከሰቱት ተቃውሞዎችና ህዝባዊ አመጾች ሳይበርዱ፣ መንግስት የጣለውን የገቢ ግብር በመቃወም ባለፈው አመት ደግሞ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች ሰፊ ተቃውሞ ተቀስቅሷል።

ይህ ከገቢ ግብር ጋር ተያይዞ የተነሳው ተቃውሞ፣ ቀደም ባሉ አመታት በተከሰቱት ተቃውሞዎች ተሳታፊ ከሆነው ህዝብ ውጭ የንግድ ማህበረሰቡ አባላትና ቤተሰቦቻቸው የተቃውሞውን ጎራ እንዲቀላቀሉ አድርጎል። ይህም በመሆኑ የተቃውሞውን ጎራ አንዲሰፋና ተጨማሪ ጥንካሬ እንዲያገኝ ያደረገ ሲሆን፣ የስርአቱ የድጋፍ ምህዳርም እጅግ እንዲጠብ ሆኗል።

በራሱ በስርአቱ ውስጥም የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ጠንክሮ የ26 አመት ጉዞውን እጅግ የሚሞግት ተግዳሮት እንደገጠመው እየታየ ነው።

በዚህ በተቃውሞ በመናጥ ላይ የሚገኘው ስርአት ከተከሰተው ሁኔታ ተምሮ የለውጥ መንገድን ከማመቻቸት ይልቅ በአብዛኛው ለውጥ በማገት ባህሪው ላይ ሲውገረገር ይታያል።

በኢህአዴግና በኢትዮጵያ መንግስት ውስጥ መሪ ሚና የሚጫወተው ሕወሀት፣ ወልቃይት ጠገዴን በተመለከተ የሚከተለው ፖሊሲ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ ለየት ያለ ነው። ይህ ሁኔታ አካባቢውን ወደ ትግራይ ክልል ከማጠቃለሉ ጋር ተያይዞ የተቀየሰ ነው። ወልቃይት ጠገዴን ወደ ትግራይ ከማጠቃለል ጋር ተያይዞ በተቀሰቀሰው ተቃውሞ ምክንያት የህወሀት ሰራዊት ባካባቢው ተደጋጋሚ ወታደራዊ እርምጃዎችን ወስዷል። በዚህም ብዙ ህይወት ጠፍቷል፣ ንብረት ወድሟል፣ ህዝብ ተፈናቅሏል።

ሕወሀት ይህን የወልቃይት ጠገዴን አካባቢ በትግራይ ስር አድርጎ ለመቀጠል ያለው እቅድ በካባቢው ቀደምት ነዋሪዎች ላይ የሚያስከትለው እንደምታ ምንድነው? ያካባቢው ነዋሪ ማንነቱን፣ ንብረቱንና መብቱን ለማስከበር በሚያነሳቸው ጥያቄዎችና ከሚያካሂደው ትግል ጋር ተያይዞስ ምን ያህል ዋጋ ሊከፈልበት ይችላል ?ህወሀት ቀጣይ በሆነ መልኩ አካባቢውን አፍኖና የሚፈልገውን ጥቅም አስጠብቆ ለመጓዝ እስከምን ሊጓዝ ይችላል ?ከሰፊ የፖለቲካ መብት ገፈፋና ረገጣ አልፎ ሰፊ የሆነ የዘር ማጥፋት/ማጽዳት ወንጀልስ ሊፈጽም የሚችልበት ሁኔታ ምን ይመስላል ? የሚሉ ጥያቄዎችን ነው ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚመረምረው።

የዚህ ጥናት አላማ ከላይ የተጠቀሰውንና ሊመጣ የሚችለውን አስፈሪ ክስተት ለማስቀረት በሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው።

ይህ ዶሴ የተዘጋጀው ካሁን በፊት ከተጻፉት የተሻለ አዲስ "ሰበር ዜና " ለማቅበር ሳይሆን፣ ከተጻፉትና ለህዝብ ከቀረቡት የማስጠንቀቂያ ደወሎች ውስጥ አንድ ተጨማሪ ድምጽ ለመሆን ነው።

ይህ ቀጣይ ጩኸት ሊመጣ የሚችለውን አሰቃቂ የዘር ማጽዳትም ሆነ የዘር ማጥፋት ተግባር ለማስወገድ ፣ ተጽእኖ ማድረግ ከቻለ አእምሮየን የሚያረካ ትልቅ ተግባር ይሆናል።

## ዘር ማጥፋት ምንድን ነው?

> ዘር ማጥፋት የሚባለው ቃል ወይም ክስተት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንደሚከተለው ተተርጉሟል፡፡
>
> ዘር ማጥፋት " የአንድን ሀገር ህዝብ፣ ወይም የአንድ ብሄርን ዘር ወይም ሀይማኖት ተከታይ ህዝብ ሆን ተብሎ በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት የሚካሄድ እርምጃ ነው"።

ይህ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው ሁለተኛውን የአለም ጦርነት ተከትሎ የጀርመን ናዚዎች አይሁድ ዘር ያላቸውን አውሮፓውያን በስልት ለማጥፋት ያደረጉትን ጭፍጨፋ ለመግለጥ የተቀረጸ ነው።

## ዘር ማጽዳት ምንድን ነው ?

የዘር ማጽዳት የሚለው ቃል በአውፓውያኑ አቆጣጠር በ1990 ወቹ በቀድሞዋ በዩጎዝላቪያ የተካሄደውን ሁኔታ ተከትሎ የተቀረጸ ሲሆን ትርጉሙም ከሞላ ጎደል የሚከተለው ነው። የዘር ማጽዳት አንድን ማህበረሰብ፣ ወይም የሀይማኖት ተከታይ ስልታዊ በሆነ መንግድ ከአንድ አካባቢ (ክልል) ማሰለቀቅን ሲያመለክት ይህም ደግሞ አካባቢውን አንድ ማህበረሰብ ብቻ የሰፈረበት ለማድረግ የሚደረግ ተግባር ጋር የተያያዘ ነው። የዘር ማጽዳት ተግባር የተለያዩ ተግባሮች ማለትም የተወሰነ ማህበረሰብ አባላትን ከአካባቢ ማባረርን፣ አንድን ማህበረሰብ ካንድ ቦታ ተፈናቅሎ ወደሌላ እንዲሄድ ተጽእኖ ማድረግን፣ ማሰፈራራትን፣ የጅምላ ግድያንና ሴቶችን አስገድዶ መድፈርን ሁሉ ያጠቃልላል።

የዘር ማጽዳት የጥቃት ኢላማ የሆነውን ማህበረሰብ የታሪክ፣ የባህልና መሰል መታወቂያዎች ወዘተ ቤታቸውን፣ ማህበራዊ ተቋማትን፣ ንብረታቸውን ፣ እርሻቸውን ታሪካዊ ሀውልቶቻቸውን ሀይማኖት ማእከሎቻቸውንና ታሪክን ለመዘከር የሚሆኑ መቃብሮቻቸውን ሳይቀር ካንድ አካባቢ በማጥፋት የሚገለጥ ነው።

የዘር ማጥፋት ወይም የዘር ማጽዳት ተግባር የታሰበበት፣ የተቀነባበረና በስልት የሚካሄድ ነው ሲባል፣ አንድ ህብረተሰብ በሌላው ላይ የሚያደርገው ዘመቻ ነው ማለት አለመሆኑን በትክክል መረዳት ተገቢ ነው። በአንድ ህብተረሰብ ውስጥ የሚገኙ ልሂቃን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ የበላይነትን ለመያዝና (ይዞ ለመቀጠል) ጥቅማቸውንም ለማስጠበቅ የሚያካሂዱት ተግባር ሲሆን፣ የተወሰነ ማህበረሰብን በሀሰት ወይም በተዛባ ትረካና፣ የተወሰኑ ስሜትን ቀስቃሽ በሆኑ የተመረጡ ታሪካዊ ግፎችና (ስሌክትድ ትራማ) ታላቅነቶች (ሴሌክትድ ግሎሪ ) ላይ በማተኮር የሚያነሳሱትና የሚያካሂዱት ወንጀል እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው። በሀገራችን በኢትዮጵያም ሁኔታ በአማራው ሆነ በወልቃይት ማህበረሰብ ላይ

የተካሄደውን የዘር ማጽዳትና ወደፊት ሊካሄድ የሚችለውን የዘር ማጥፋትም ሆነ ቀጣይ የዘር ማጽዳት፣ በጅምላ አንዱ ወይም ሌላው ብሄረሰብ/ ማህበረሰብ ይፈጽማል ማለት ሳይሆን፣ ለማሳየት የሚሞከረው ገዥዎች የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅመው ሊያካሂዱ የሚችሉትን የግፍ ተግባር መሆኑን ነው ።

በሀገራችን የህወሀት ኢህአዴግ አገዛዝ ፍጹም አምባገነን መሆኑንና ስልጣኑን ለማካፈልም ሆነ ለመልቀቅ ከቶውንም የማያስብ መሆኑን በጉልበትና በፍጅትም የሚችለውን ሁሉ አድርጎ በስልጣኑ ላይ ለመቆየት ጥረት ማድረጉን እንደሚቀጥል የተለያዩ ጸሀፊዎችና የፖለቲካ ተንታኞች በሰፊው አቅርበዋል።

ህወሀት መራሹ ኢህአዴግ በወልቃይት ጠገዴ የዘር ማጥፋት ወይም ዘር ማጽዳት ወንጀል ፈጽሟልን? በቀጣይነትስ ሊፈጽም ይችል ይሆን? የሚለው ጥያቄ ሰብእና የሚሰማውን ወገን ሁሉ የሚያሳስብ ነው። ይህን ለመመርመር በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የዘር ማጥፋትና ማጽዳት አደጋ ዝግጅትና ተግባር ምልክቶችን መሰረት በማድረግ እነዚህ ሁኔታዎች መኖር አለማኖራቸውን በተጨባጭ ከፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ፣ ስለልቦናዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ወታደራዊ ዝግጅቶችና ተግባር ጋር በማያያዝ ምርመራ ይካሄዳል።

በመጨረሻም ሁኔታውን ለማምከን ምን መደረግ እንዳለበት ሀሳብ ይቀርባል።

***ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመግባቴ በፊት፣ በዚህ ጽሁፍ የቀረበው መረጃም ሆነ ሀተታ ሁሉ ህወሀትንና መሪዎቹን አንደድርጅትና እንደተቋም የሚመለከት እንጂ ሰፊውን የትግራይን ህዝብ አለመሆኑን በግንዛቤ ውስጥ እንዲያዝ ማሳሰብ እወዳለሁ።***

# የአደጋው መሰረቶችና ምልክቶች

## የአደጋው ኢኮኖሚያዊ መሰረት

### ከፍተኛ የንብረት (የሀብት) ጠቀሜታ መኖር

በ አንድ አካባቢ የዘር ማጥፋትን አደጋ ከፍ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ይህን ተግባር በመፈጸም ሊገኝ የሚችል የንብረት፣ ክምችት ወይም የጎላ የሀብት ጠቀሜታ መኖር ወይም አለመኖር ነው። የሚገኘው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ከፍ ያለ ሲሆን አደጋውንም ሰፊ ያደርገዋል። የዘር ማጽዳትም ሆነ የዘር ማጥፋት ከፖለቲካና ማህበራዊ መሰረቶች በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ መሰረቶችም አሉት ።

በአልበሽር የሚመራው የሱዳን መንግስት በምእራብ ሱዳን በዳርፉር የነዋሪዎቹን መሬት ለመንጠቅና ተቃዋሚዎቹንም ለማጥፋት የጃንጃዊድ ሚሊሻዎችን አስታጥቆ እንዳሰማራና ከፍተኛ የዘር ማጥፋት እንዳካሄደ ይታወቃል።

በሀገራችን ሁኔታ በተለይ በሰሜን ምእራብ በወልቃይት ጠገዴ የምንመለከተውም ይህንኑ ነው። በዚህ አንጻር ህወሀት የፖለቲካ መሪዎች ወልቃይት ጠገዴ ጋር ያላቸውን የኢኮኖሚ ጥቅምና ቁጥጥር በመጠኑ ከዚህ በታች ቀርቧል።

### ሰፊና ለም ግዛት

በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1990ዎቹና በ2000ዎቹ በደቡብ ሱዳን ለም ምድርና የነዳጅ ሀብትን ለመንጠቅ በምእራብ ሱዳን ደግሞ የዳርፉር ገበሬዎችን መሬት ለመንጠቅ በጃንጀዊድ ሚሊሻዎችና በሱዳን መንግስት የጸጥታ ሀይሎች ትብበር አሰቃቂ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንደተካሄደ ታሪክ መዝግቦታል።

ወልቃይት ጠገዴን ስንመለከት ደግሞ ይህ አካባቢ ሰፊ ግዛት ብቻ ሳይሆን ብዙ ህዝብ ያልሰፈረበት ባለብዙ ሀብት ምድር በመሆኑ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያሰገኛል።

የወልቃይት ጠገዴ አካል የሆነውና **ቃፍቲያ** ሁመራ እየተባለ የሚጠራው ወረዳ ብቻ የቆዳ ስፋቱ 717,657 ሽህ ካሬ ሜትር ነው። ይህ ምድር በልማት በኢትዮጵያ ውስጥ ምርጥ ከሚባሉትና በእርሻ ረገድም በጥጥ፣ በሰሊጥ፣ በኑግ በዘንጋዳ ምርት ወዘተ እጅግ ከከበሩት ቦታዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚጠራ ነው።

የመሬት ይዞታንና የህዝብ ብዛትን ስንመለከት ከአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ 1991 ወዲህ ወደ ትግራይ እንዲካለል በሆነው በቃፍቲያ ሁመራ የሚኖረው የህዝብ ብዛት በአንድ ስኩየር ኪሎ ሜትር 12.3 ሰው ነው ። ባንጻሩ በአጠቃላይ በትግራይ ውስጥ ደግሞ በማከላዊነት በአንድ እስኩየር ኪሎ ሜርት 91.2 ሰው ይኖራል። ባንድ ስኩየር ኪ.ሊ ሜትር በቃፍቲያ ሁመራ ከሚኖረው በሰባት እጅ የበለጠ ህዝብ ማለት ነው።. በተለይም በአድዋ አውራጃ በላይኛው ማይጨውና ራያ በስኩየር ኪሎ ሜረት 250 ሰው ይኖራል። በነዚህ አውራጃዎች ደግሞ ከቃፍቲያ ሁመራ ጋር ሲወዳደር ሀያ እጥፍ ህዝብ ባንድ እስኩየር ኪሎሜትር ይኖራል ማለት ነው።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው መረጃ ወልቃይት ጠገዴ በመሬት ጥበት እጅግ እየተጨነቀች ለነበረችው ትግራይ የሚያሰገኘውን ከፍተኛ ጠቀሜታ (ያውም ለም መሬት) በግልጥ ያሳያል።
http://www.ethiodemographyandhealth.org/Tigray.html

**<u>ለደጋፊዎች እጅግ ሰፋፊ የግል ይዞታ መስጠት</u>**

የግለሰብ የመሬት ይዞታን በተመለከተ ደግሞ ቃፍትያ ሁመራ ባውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1992 ጀምሮ የሰፈሩት ከሱዳን የተመለሱም ይሁን ሌሎች የተሰጣቸውን መሬት ሰፋት በትግራይም ይሁን በመላ ኢትዮጵያ ከሚገኙ የገበሬዎች የእርሻ መሬት ስፋት ጋር ስናወዳድረው አካባቢውን " በታማኞች " እንዲያዝና ባጠቃላይም ወደትግራይ የማጠቃለሉ ጥቅም ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ መመልከት ያሰችላል።

በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 ማለትም (በኢትዮጵያ 2005)፡ የኢትዮጵያ የጠቅላይ እስታትስቲክስ ጽህፈት ቤት ባቀረበው መረጃ መሰረት በሀገራችን የሚታየው አማካይ የገበሬው የመሬት ይዞታ እንደሚከተለው ነው።

| | ኦሮሚያ | ደቡብ | አማራ | ትግራይ | አጠቃላይ ኢትዮጵያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| **ማከላዊ የእርሻ ይዞታ ሰፋት በሄክታር (በቤተሰብ)** | **1.15** | **0.49** | **1.09** | **0.91** | **0.96** |
| | | | | | |
| **ይዞታቸው ከግማሽ ሄክታር በታች የሆኑ ገበሬወች %** | **30.0** | **61.7** | **33.4** | **41.4** | **39.7** |
| | | | | | |

መረጃ ከ . Farm distribution by major highland regions, 2011–2012. (*Nationally representative statistics from Central Statistical Agency (2012)* )

**በቃፍትያ ሁመራ የሰፈሩ ግለሰቦች የተሰጣቸው መሬት ስፋት ደግሞ እንደሚከተለው ነበር**

| | |
|---|---|
| አንድ ሰው (ሌጣ) | 1 ሄክታር |
| ከሁለት እስከ ሶስት ሰው ያለው ቤተሰብ | 2 ሄክታር |
| አራት ወይም ከዚያ በላይ ሶስት በላይ ቤተሰብ | 3 ሄክታር ነበር |
| | |

ከዚህ በተጨማሪም ለሁሉም ሰፋሪ የቤት መስሪያ ተብሎ ለያንዳንዶ 1000 ካሬ ሜትር ቦታ በነጻ ተሰጦቷል። ይህ ይዞት ባጠቃላይ በትግራይም ይሁን በመላ ኢትዮጵያ ከሚታየው የገበሬው የመሬት ይዞታ ጋር ሲወዳደር ለወልቃይት ሰፋሪዎች የተሰጠው እጅግ ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን ከሁለት እሰከ ሁለት ተኩል እጅ እጥፍ እንደሆነ እናያለን። በቃፍትያ ሁመራ የሰፈሩ ሁሉ ዝቅተኛ ይዞታቸው ለአንድ ግለሰብ አንድ ሄክታር እንደሆነ ስንመለከትና ከግማሽ ሄክታር በታች ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች በኦሮሚያ 30% በደቡብ 61% በአማራ 33.4% በሌላው ትግራይ ውስጥ 41.4% እንደሆኑ ከላይ በቀረበው መረጃ ስናይ ደግሞ የወልቃይት ጠገዴ ግዛት በግለሰብም ደረጃ ምን ያክል የኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንደሚያሰገኝ ለመረዳት አይከብድም።

ይህ ብቻ አይደለም፣ በቦታው ከሰፈሩት የሱዳን ተመላሾች ውስጥ ገንዘብ አለን ለሚሉ ደግሞ ከአራት ሄክታር እስከ አስር ሄክታር መሬት በነጻ የተሰጣቸው እንዳሉም ይታወቃል። ይህ ሁሉ የኢኮኖሚ ጥቅም ህወሀት ታማኝ የሆኑ የጥፋቱ አስፋጻሚዎችን ለማፍራት አግዞታል። ስለሆነም በህወሀት መሪነት በወልቃይት የተካሄደው ተራ የሰፈራ ተግባር ብቻ ሳይሆን፣ የፖለቲካ ስልጣንን የመንከባከብና ከጥቃት የመጠበቂያ ሀይል ግንባታም ጭምር እነደሆነ እናያለን።

(ካሳሁነ ብርሃኑ፣ **Kassahun Berhanu,** Returnees, Resettlement and Power Relations; the making of political constituentncy in Humera, Ethiopia, Amsteredam, 2000, pp 159-162)

ይህን ሁሉ አጠቃለን ስንመለከት ይህ ለም ምድር በለምነቱና በሚያሰገኘው ጠቀሜታ የተነሳ ባካባቢው ላይ የይገባኛል ጥያቄን የሚያነሱ ነባር ነዋሪዎች ህልውና ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ አደጋ ላይ እንደሆነ ያመለክተናል።

**የህወሀት ዘመናዊ የእርሻ ኢንደስትሪ ንብረት ከምችት**

የወልቃይት ጠገዴ አካባቢ በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ህወሀትን እንደተቋም የከፍተኛ የንብረት ባለቤት ያደረገ ከፍተኛ የገቢ ምንጭም ነው። ለዚህ አንዱ ምሳሌ የህወሀት ሀብት የሆነው የህይወት ሜካናይዝድ እርሻ እንዱስትሪን ሁኔታ መመልከት ተገቢ ነው።

የህይወት ሜካናይዝድ እርሻ ተቋም ወደ ወልቃይት ብቅ ያለው ህወሀት አዲስ አበባ ላይ ስልጣን ከያዘና በሁመራ አካባቢም ሰፈራ ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ ነው።

በውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1992 የህወሀት የኢኮኖሚ ክፍል አንዱ አካል የሆነው ህይወት መካናይዝድ የእርሻ ኩባንያ በደርግ ጊዜ "የሁመራ መንግስት እርሻ" ተብሎ ይጠራ የነበረውን 10, 000 (አስር ሽህ) ሄካታር መሬት ተሰጠው። በዚህም የጥጥ፣ ሰሊጥና ዘንጋዳ እርሻውን በተደላደለና ከ100 በላይ ትራክተሮችና 4000 ሰራተኞች ወርሶ ስራ ጀመረ (Kassahun Berhanu,, 2000 )

በህይወት ሜካናይዝድ እርሻ እንዱስትሪ ድረ ገጽ እንደተገለጸው ደግሞ ከሰፊው የእርሻ መሬት በተጨማሪ የእንስሳ እርባታ ራውያን  በተሰኘው በዚሁ በቃፍትያ ሁመራ ወረዳ  ያካሂዳል።

የህይወት ሜካናይዝድ እርሻ እንዱስትሪ  ንብረት ከሆነው ሰፊ የእንስሳት እርባታ በተጨማሪ፣ ሕይወት እርሻ በቦታው ከደረሰ ወዲህ የሚከተለውን ተጨማሪ የኢርሻ መሬት ይዟል።

- በከባቦ እርሻ (Kebabo )፡ 2400 ሄክታር .
- ባናት እርሻ (Banat Farm) : 3096 ሄክታር .
- ንጓራ እርሻ ( Niguara Farm)  2382 ሄክተር መሬት እርሻ እንደያዘ ያሳያል።

http://effortinvestments.com/new/index.php/companies/agriculture/hiwot-agricultural-mechanization

ሕይወት እርሻ መካናይዜሽን ኢንዱስትሪ የህወሀት የግል ንብረት ከሆኑት የተለያዩ ኩባንያዎች አንዱ ነው። ከላይ የተመለከቱት መረጃዎች ባጠቃላይ አካባቢው ለህወሀት ታማኝ ለሆኑ ወታደሮችና ሰፋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለድርጅቱ ለህወሀትም በግል ከፍተኛ የሀብትና የገቢ ምንጭ እንደሆነ ያሳየናል።

**እጅግ ሰፊ የሰሊጥ ምርትና መጠነ ሰፊ ገቢ**

የሰሊጥ ምርት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት ሰብል ነው። በወልቃይት ጠገዴ የሚመረተው ነጭ ሰሊጥ ደግሞ በተለይም በአለም ገበያ እጅግ ተወዳጅነት ያለው ምርት ነው ።

በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2013 በቀረበ  ከዚህ በታች በተመለከተው ጥናት መሰረት በወልቃይት ጠገዴ የሚመረተው የሰሊጥ ምርት ግምት የሚከተለው ነው።

| ወረዳ | የእርሻ ቦታ ስፋት በሄክታር | ሰሊጥ እርሻ ስፋት | አጠቃላይ ምርት | ምርት በሄክታር | |
|---|---|---|---|---|---|
| ወልቃይት | 64,160 | 25,796 | 189,292 | 7.34 | |
| ጠገዴ | 96,129 | 32,735 | 198,905 | 6.00 | |
| ቃፍትያ ሁመራ | 376,398 | 222,575 | 1,386,143 | 6.23 | |
| ጠቅላላ | 536,685 | 281,105 | 1,774,340 | 6.30 | |

Table1፡ sesame Business Network (SBN) sesame Business Network (SBN) sesame Yield and Post harvest Losses in North west  Ethiopia, October – January 2013 http://sbnethiopia.org/wp-content/uploads/2014/06/Sesame-Yields-and-Post-harvest-loss.pdf

የሰሊጥ ንግድ ኔት ወርክ  በፌበርዋሪ 2017 ባወጣው መረጃ መሰረት ይህ ምርት ረከሰ በተባለበት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2016 ዓ.ም. በኩንታል ከ 1500 እስከ 1700 ብር ይሸጥ ነበር። በፌበርዋሪ 2017 ደግሞ ዋጋው በኩንታል 2500 ደርሷል።

https://www.agriterra.nl/upload_dir"ectory/files/SBN_Ethiopia_Newsletter_13_February_2017(2).pdf

በዚህ ስሌት ወልቃይት ጠገዴ (በህወሀት ኩባናያና ኢጋር ኢንቨስተሮች ጨምሮ የሚያሰገኘውን ገቢ እንደሚከተለው ይሆናል ለዚህ ጉዳይ የዋለው  281,105 ሄታር እርሻ በሄክታር 6.30 ኩንታል ያመርታል ብለን ብናሰላ  አጠቃላዩ ምርት የሚሆነው 1, 774, 340 ኩንታል  ነው። የአንድ ኩንታል ሰሊጥ ዋጋ ደግሞ በአማካኝ 2000 (ሁለት ሽህ ብር ) ብለን ብንወስድ የሚገኘው አመታዊ ገቢ እንደሚከተለው ይሆናል።

1,774,340 ክንታል  X ብር 2000 በኩንታል= 3,458,680,000 ብር(ሦስት ቢሊየን አራት መቶ ሀምሳ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሽህ ገቢ በአመት ያሰገኛል ) ማለት ነው። ይህን  ገንዘብ ወደ አሜሪካን ዶላር ለመቀየር አሁን ባለው ከፍተኛ ዋጋ  አንድ ዶላር ለ27 የኢት ብር ሂሳብ ስናሰላው  $127,659,878.80 ( አንደ መቶ ሀያ ስባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ  ሺህ ስምንት መቶ ስባ ስምንት የአሜሪካ ዶላር)  ይሆናል።

ይህ ከላይ የተገለጠው ጥቅም የወልቃይት ጠገዴ ምድር ባሁኑ ሰአት በየአመቱ ከሰሊጥ ምርት ብቻ leh ለህወሃትና ለደጋፊዎቹ የሚያሰገኘው ገቢ  ነው።

ከህይወት መካናይዝድ እርሻ በተጨማሪ በመቶዎች የሚቆጠሩ በድርጅቱ ፋይናንስ እየተደጎሙ ባካባቢው የሰፈሩና ሰፋፊ የእርሻ ይዞታ የተሰጣቸው " ኢንቨስተሮች" መኖራቸውን በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው።

ህወሀት ባካባቢው ቁጥጥሩን አጠናክሮ እስከቀጠለ ደግሞ ወልቃይት ጠገዴ አሁን ከሚያገኘው በብዙ እጅ እጥፍ ድርብ የሆነ ገቢ እያሰገኘው እንደሚቀጥልና ከፍተኛ የሀብት ምንጩ እንደሚሆን ያውቃል፡፡ በነገራችን ላይ እርሻና ከብት እርባታውን ሕይወት የተሰኘው የህወሀት ኩባንያ ሲቆጣጠር ያካባቢውን ንግድ ደግሞ (የሰሊጥ ንግዱን ጨምሮ) ጉና የተሰኘው ሌላው የህወሀት ኩባንንያ ነው የሚቆጣጠረው።

ባጠቃላይ ወልቃይት ጠገዴ በለምለምንቱ የተነሳ ሰፊ ገቢ ሊያሰገኝ የሚችል ምድር መሆኑ ታላቅ ጸጋ መሆን ሲገባው የህወሀትን አልጠግብ ባይ የማይረካ የንብረትና ሀብት የማካበትና ሌሎችን ተጭኖ ከመኖር ፍላጎት የተነሳ ለአካበባው ቀደምት ነዋሪዎች ህልውናቸውን የሚያሳጣ የከፍተኛ አደጋ ሰለባ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

የአካባቢውን ከህወሀት ቁጥጥር ውጭ መውጣት ህወሀት በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ በሚቆጣጠራቸው ኩባንያዎቹ የሚያገኘውን ከፍተኛ ገቢ እንዳጣ ያደርገኛል በሚል እሳቤ ይህን ጥቅሙን ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሞት የሽረት ትግል ማካሄዱ ብቻ ሳይሆን ይህን ጥቅም ያጸረራሉ ብሎ ከሚገምታቸው የወልቃይት ጠገዴ ነባር ህዝብ አካባቢውን የማጽዳት አደጋ እጅግ ከፍተኛ ነው።

ይህ አደጋ መሰረት የሌለው ባዶ ፍራቻ ላይ ብቻ የተመሰረተ ላለመሆኑና ሕወሀት ወልወቃይትን ይዞ ለመቆየት ሲል ሊወስድ የሚችለውን አደገኛ እርምጃ ከሚያመለክቱ ብዙ መረጃዎች ውስጥ የህወሀቱ የወቅቱ ሊቀመንበር የዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል የፌስ ቡክ መልእክት እንደሚከተለው ይነበባል።
"DR DEBRETSION GEBRE MICHAEL
August 31, 2016 ·

> *በአማራ ክልል የተከሰተው ረብሻ ከቀን ወደ ቀን ኢድማሱን እያሰፋ ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ መምጣቱን እያየን ነው። ይህ እየሆነ ባለበት ሁኔታ እንኳን፣ መንግሥት የማረጋጋት ሥራውን በከፍተኛ ጥንቃቄና ትግስት እያከናወነ ይገኛል።ይህ ትግስታችን ግን እንደ ደካማነት በመቆጠሩ ብጥብጡ እጅግ የከፋ ወደሆነ አቅጣጫ እንዲያመራ አድርጎታል። መከላከያችን አመፆች በሚነሡበት ጊዜ ጉዳዩን በትግስት የመቆጣጠር ግዴታ ያለበት በመሆኑ ነው እንጂ እንኳንስ 30 ሚሊዮን ሕዝብ አይደለም የመላው አፍሪካን ሰላም ለማረጋጋት አቅም እንዳለው የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ያረጋገጡት ሃቅ ነው። ሆኖም በዚህ ኃያል አቅሙ ሳይኩራራ ነገሮችን በብስለትና በትግስት ሲያከናውን ቆይቷል።የእስካሁኑ ትግስታችን ግን ብዙ ጥፋቶች እንዲካሄዱ በር እየከፈተ በመሄዱ የመከላከያ ኃይላችን በከፍተኛ ዲሲፕሊን በመሆን ብጥብጡ ወደከፋባቸው አካባቢዎች በመሄድ አስፈላጊውን የማረጋጋት እርምጃ እንዲወስድ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ታዟል። ድል ለመከላከያ ሠራዊታችን!"*

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የአማራውን ህዝብ በተለይም የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ ላይ ህወሀት ለመውሰድ የተዘጋጀውን እርምጃ ዶክተር ደብረጽዮን (""Dr Debretsion Gebre Michael June 30 · ) በፌስ ቡክ ላይ በጁን 30 2017 ( በአውሮፓ አቆጣጠር) የሚከተለውን አሰፍረዋል ፡

> *"ለኦሮሚያ ሕዝብ ጥያቄ በአዲስ አበባ የልዩ ተጠቃሚነት ዐዋጅ በመደንገግ ለሕዝቡ ምላሽ እየተሰጠ በሚገኝበት በዚህ ሰዓት፤ በተመሳሳይ መንግሥት ይህንን ዓይነት መፍትሔ ለአማራ ክልልም እንደሚሰጥ በመጠበቅ ላይ ይገኛል። ሆኖም አንዳንዶች እንደሚጠብቁት ወልቃይትን ለአማራ በመመለስ፤ መንግሥት ከአማራው ጋር ለመታረቅ እየጣረ ነው የሚለው አመለካከት ፍፁማዊ ስህተት ነው። አዲስ አበባን ለኦሮሚያ ስንፈቅድ የራሳቸው ክልል ላይ የሚገኝ መሬት በመሆኑ ነው እንጂ ከሌላ ክልል ወስደን አልሰጠንም። በመሆኑም ወልቃይትን ከትግራይ ነጥቀን ለአማራ የምንሰጥበት ምንም አግባብ አይኖርም። ይህን ዓይነት አመለካከት የሚያራምዱ ጥቂት ጸረ-ሕዝብ ኃይሎችን ለመቅጣት መከላከያችን ሁሌም በንቃት በመጠባበቅ ላይ የሚገኝ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ። ድል ለሰፊው ሕዝብ! """Dr Debretsion Gebre Michael June 30 ·*

## ፖለቲካዊ ገጽታ

ህወሀት በወልቃይት ጠገዴ ያደረገውን እና ሊያደርግም የሚችለውን የዘር ማጽዳት እርምጃዎች ለመገንዘብ የሚከተሉትን ቁልፍ የፖለቲካ ሁኔታዎች በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡

- ህወሀት አዲስ አባባ ላይ ስልጣን ከያዘ በኋላም እንኳ ራሱን የሚጠራው በትግራይ ነጻ አውጪነት መሆኑ የፖለቲካ መሰረቱን ምንን አድርጎ ለመቀጠል እንዳቀደ አመላካች ነው። በሀገሪቱ ፖለቲካ ማህደር የበላይነቱን ይዞ ለመቀጠል የሚያደርገውን ሙከራ ማስቀጠል የሚሻው የፖለቲካ መሰረቱን ባንድ ብሄር ላይ በማድረግ ነው።

- 'ለ26 አመታት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ብዙሀዊነትን እቀበላለሁ ይበል እንጂ በተግባር ግን የፖለቲካ ስርአቱ የህወሀትን የበላይነት በሚያረጋግጥ መልኩ የተደራጀ ነው።

- ተቃዋሚ ድርጅቶች ተራ በተራ ህልውናቸው እንዲያከትም የተደረጉ ሲሆን በ ኢህአዴግም ውስጥ ህወሀት አሁንም ቁልፍ የወሳኝነት ቦታውን እንደያዘ ይገኛል።ህወሀት/ ኢህአዴግ በስልጣን ላይ በቆየባቸው 26 አመታት ለማንኛውም ተቃውሞ ያለው ርህራሄ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ በተደጋጋሚ ታይቷል። የረዥም ጊዜ ታሪኩ የሚመሰክረው የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን፣ መሪዎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በመግደል፣ በማሰር፣ መዳረሻቸውን በማጥፋት... ወዘተ ሙሉ በሙሉ ሀይልን ተጠቅሞ የመደምሰስ ታሪክን ነው።

- ህወሀት ጠንከር ያለ ተቃውሞ በሚገጥመው ቦታ ሁሉ ተቃዋሚውን ለማጥፋት የጅምላ እስራትና ጭፍጨፋ ያካሄዳል። በአዲስ አባባ ምርጫ 97ን ተከትሎ ያካሄደው የ200 ግለሰቦችን ህይወት ያጠፋው ጭፍጨፋ፣ በኦጋዴን በተከታታይ ያካሄደው መንደርን ሙሉ በሙሉ እስከማውደም የደረሰ ጭፍጨፋ ፣ በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ከተሞች የተቃውሞ ሰልፎች ላይ የወሰደው ግድያን፣ ያስከተለ ጭፍጨፋ ወዘተ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።
- በሌላ በኩል ደግሞ ስርአቱ ተግባራዊ ባደረገው የብሄር ተኮር የክልሎች አሸናሸንና የመሬት ባለቤትነትን ለየክልሉ ነዋሪዎች ብቻ በባለቤትንት የሚሰጠውን የስርአቱን ፖለቲካዊ መመሪያ በተጎራባች ድንበርተኛ የሚኖሩ ዜጎችን ለረጅም ጊዜ ያገኙት የነበረውን ጥቅማቸውን በማገድ ከፍ ወዳለ መከፋትና ቅራኔ እንዲገቡ ይገፋፋል።

- የሀገራችን ህዝብ 80% በላይ በእርሻ በሚተዳደርበት ሁኔታ መሬት እጅግ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ንብረት ነው። መሬትን ለክልሉ ነዋሪዎች ብቻ ያደረገው የስርአቱ ፖሊሲ፣ እያንዳንዱ ክልል ፣ ሰፋ ያለ ክልል እንዲኖረው መሞከር ብቻ ሳይሆን የክልል ድንበር ጉዳይ ከፍተኛ ህይወትን የቀጠፈ፣ ዜጎችን ያፈናቀለ፣ የግጭት መሰረት እንዲሆን አድርጎታል ። በኦሮሚያና በሶማሌ ክልል፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልል፣ በአፋርና አማራ ክልል፣ በኮንሶ፣ በኦሮሚያና በቤነሻንጉል ክልል፣ በጉጂና በቡርጂ ማህበረሰቦች መካከል ወዘተ የተከሰቱት ግጭቶች ለዚህ ማሳያ ናቸው።
- የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት ካመሰራረቱ ጀምሮ በዋናነት የህወሀት ሰራዊት መሆኑ፣ የሰራዊቱ መሪዎችም የፖለቲካ ድርጅቱ አባል መሆናቸው የፓርቲውን (የህወሀትን) ትእዛዝ ለማስፈጸም (በህዝብ ላይ ጥፋት ለመፈጸም) እጅግ የተመቻቸ አድርጎታል ።

ወልቃይት ጠገዴን በሚመለከት የሚነሳ ተቃውሞ ከላይ የተመለከቱት የህወሀት መሰረታዊ ጠቀሜታዎች ጋር የተጻረረ ነው። ሕወሀት በወልቃይት ጠገዴ የሚነሳውን ተቃውሞ እንዴት ሊያስተናግደው እንደሚችል ለመመርመር ሲሞከር እነዚህን እውነታዎች በግንዛቤ ውስጥ ማስገባትን ይጠይቃል።

## ጠንከር ያለ የተቃዋሚ ሀይል ከመኖር ጋር የተያያዘ አደጋ

የዘር ማጥፋት/ ዘር ማጽዳት ከሜደ ተነስቶ በድንገት ወይም በግብታዊነት የሚካሄድ ሳይሆን በጥናት በእቅድና በስልት ተቀነባብሮ ሆን ተብሎ የሚካሄድ የጭካኔ እርምጃ ነው።

በቅርብ በተካሄዱ ጭፍጨፋዎች ማለትም በቦዝንያ፣ በርዋንዳ፣ በዳርፉር፣ በሊቢያና በሶርያ ታሪክ እነደሚያሰረዳን፣ በስልጣን ላይ የሚገኝ አምባገነን መንግስት ለህልውናው አስጊ ሁኔታ ሲፈጠርና በተለይም ደግሞ በጦርነትና በተፋፋመ ውጊያ ጊዜ ተቃውሞውን ለማፈን ሲል የስጋቱ መሰረት ነው ብሎ የሚያሰበውን የህብረተሰብ ክፍል የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳትን የሚጨምር ከፍተኛ ጥቃት ሊፈጽምባቸው ይችላል።

ይህ እውነታ የዘር ማጥፋት በተካሄደባቸው የተለያዩ ሀገሮች የታየ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በሩዋንዳ በአውሮፓውያን ቀቆጣጠር በ1994 የተካሄደው ጭፍጨፋ አር ኤፍ ፒ (RPF )የተሰኘው በአብዛኛው የቱትሲ (Tutsi) ብሄረሰብ አባላትን ያቀፈው የተቃዋሚው ድርጅት ታጣቂ ሀይል ጥንካሬ እያገኘና በስልጣን ላይ የሚገኘውን መንግስት (Hutu) መፋለም ሲጀምር የዘር ማጽዳቱ አደጋም እጅግ እየተጠናከረ እንደመጣ ታሪክ ያሳያል። በደቡብ ሱዳን የሱዳን መንግስት ተቃዋሚው ኤስፒኤልኤን (SPLA) በዳርፉር ምእራብ ሱዳን ተቃዋሚዎቹን የሱዳን ነጻነት ንቅናቄ እንዲሁም የፍትህና የእኩልነት እንቅስቃሴን (Sudanese Liberation Movement (SLM), and the Justice and Equality Movement (JEM) ለማጥፋት በወሰደው እርምጃ፣ አጠቃላይ የዘር ማጽዳት ተግባር ውስጥ ተሰማርቷል። በሊቢያና በሶርያም የታየው ይኸው እውነታ ነው።

በወልቃይት ጠገዴ የሚታየው ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ብዙ የሚያመሳስለው ጉዳይ አለ።

የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪ ህዝብ ገና ከመጀመሪያው ለህወሀት መስፋፋት በእምቢተኛነት አልቀበልም ባይነትን አሳይቷል። ህወሀት አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ አካባቢውን ወደትግራይ አካልነት ካዛወረ ጊዜ ጀምሮም ተቃውሞው በሰፊው እንደቀጠለ ነው። ይህ ተቃውሞ አንዴ ሲጠነክር ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲቀዘቅዝ ቆይቶ በ2007 ዓ.ም በሌ/ ኮሊኔል ደነቀ እና ሰፋ ባሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ግንባር ቀደምትነት “የወልቃይት የአማራ ማንንተ ጥያቄ” እና “ጎንደር ህብረት ለኢትዮጵያ አንድነት” “ በሚል ስም ተጠናክሮ በመውጣት ሰፊ የመብት ማስከበር እንቅስቃሴን በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ይህን የተቃውሞ ንቅናቄ ገና ከጅምሩ በ እንጭጩ ለማስቀረት የትግራይ ክልላዊ መንግስትና ህወሀት መራሹ ፌደራላዊ ሀይል እጅግ ሰፊ ወታደራዊ ዘመቻ አካሂዷል። ተቃውሞውም ከአካባቢው ህዝብ የማንነት ጥያቄ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ስርአቱ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ በሀይል ለመደምሰስ መርጧል። መሪዎችን አስሯል፣ በእስር ላይም እጅግ የከፋ ስቃይ አድርሶባቸዋል።

http://www.satenaw.com/amharic/archives/41500

ተቃዋሚውን ለማጥፋትም ታጋዮችን ይደብቃሉ፣ ይደግፋሉ፣ ያሰተናግዳሉ የሚባሉትን አካባቢዎች በከፍተኛ ወታደራዊ ሀይል ማንበርከክ ህወሀት መራሹ መንግስት የመረጠው አካሄድ ሲሆን፣ ውጤቱም በወልቃይትና ጎንደር የአማራ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረና የተቀነባበረ ጥቃት ሆኗል።

የአካባቢው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መካሄድ በጀመረበት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2008 እና 2009 አመት ምህረት፣ ህወሀት ተቃውሞውን ለማፈን ምን ያክል ርቆ ሊሄድ እንደሚችል የሚያሳዩ የተለያዩ መረጃዎች ተከስተዋል።

እነዚህ እርምጃዎች በህወሀት ቁልፍ የፖለቲካ ሹሞች ከሚቀርቡ ታሪክን የማጣመም ፕሮፓጋንዳ እስከ ማስፈራሪያና በአካባቢው በሰፈራ ስም የተሰማሩ ወታደሮችን የእርሻ መሳሪያቸውን ወርውረው ክላሽናኮቭና ባዙቃ ተሸክመው በአካባቢው ነባር ነዋሪ ወልቃይቴዎች፣ አማራዎች / ጎንደሬዎች ላይ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እስከመዝምት የሚደርሱ እርምጃዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። ለዚህም የሚከተሉትን እንመልከት

DR DEBRETSION GEBRE MICHAEL

April 3 ·

> ”የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጁ በመራዘሙ ደስታቸውን የገለጹ እንዳሉ ሁሉ፣ የዜጎችን መብት ይገፈፋል በሚል ሥጋት የተቃወሙም አልጠፉም። የህገሪቱ ሰላም ሙሉ በሙሉ ሲረጋገጥና ወልቃይት ጠገዴ ወደ አማራ ክልል መካተት አለበት የሚሉ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ተገቢውን ቅጣት ካገኙ በኋላ፤ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጁ አራት ወር ሳይቆይ እንደሚነሣ ሙሉ ተስፋ አለኝ”።

በተደጋጋሚ በመሪዎቹና በድርጅቱ በራሱ እንደተገለጠው ህወሀት ኢህአዴግ “ትምክተኛ ሀይሎች ወይም ትምክተኛ ሲል” አማራ ማለቱ አንደሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚገነዘበው ትርጉም ነው። በ አማራው ማህበረሰብ ውስጥ የሚካሄድ የመብት ትግል በስርአቱ የሚተረጎመው እንደመብት ጥያቄ ሳይሆን “ያለፈውን ጨቋኝ የአማራ ገዥነት እንደገና ለመመለስ የሚደረግ ትግል” “ህገ መንግስቱን ለማፈራረስ”፣ “የብሄር ብሄሩሰብን መብት ለማፈን የተደረገ” ተደርጎ ነው። የስርአቱ መሪዎች ይህን ይመኑበት አይመኑበት በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚያቀነቅኑት በብሄር ላይ የተመሰረተውን ቅኝት ነው። ይህ እኛና እነሱ የሚለው እምነታቸው በአካባቢው የሚነሳ የህዝብ ንቅናቄን የሚመለከቱበትን መሰረታዊ እይታ ያሳያል። በወልቃይት ጠገዴ የሚካሄደውንም ማንኛውንም የማንንት ንቅናቄ ህወሀት የሚመለከተው ትግራይን ለመጉዳት ፣ እንደተነሳ፣ ጸረ ሰላም “የትምክተኞች “ ሴራ ነው። ለዚህ ደግሞ መፍትሄው ከላይ በዶክተር ደብረጽዮን እንደተገለጠው “ ወልቃይት ጠገዴ ወደ አማራ ክልል መካተት አለበት የሚሉ ፀረ-ሰላም ኃይሎች “ ተገቢው ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ነው ይህ ብቻ አይደለም በአካባቢው የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ ለማጥፋት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2009 በተደረገው እንቅስቃሴ ሕወሀት ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ በአካባቢው ያሰፈራቸው ሰፋሪዎች መሳሪያ አንስተው እንዲፋለሙና የመብት ጥያቄ ባነሱት ላይም አዲሱ ሰፋሪ ራሱ ተነስቶ እንዲዘምትባቸው፣ እንዲያዋርዳቸው፣ የሚያደርግ ስነልቦናዊ ተጸእኖ አካሂዷል። የዚህ ስነልቦናዊ ተጽእኖ አላማ አንድም በመፍራት፣ በመደናገጥና መጭውን አደጋ በመገንዘብ አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ ማድረግ ሲሆን ይህ ሳይሆን ደግሞ ቀሪዎቹ ቋሚ የሆነ የስነልቦና ስብራት እንዲደርስባቸውና ምንም አይነት የመብት ጥያቄ ከማንሳት እነዲታቀቡ ለማድረግ ነው ።

ይህ የስርአቱ አካሄድ፣ በተቃውሞ እንቅስቃሴው ውስጥ የተሰለፉ ወይም ይህን እንቅስቃሴ የሚደግፉ ሁሉ ለመብታቸው መከበር የቆሙ ሳይሆኑ የሌላውን መብትና ህልውና አደጋ ላይ ለመጣል የተነሱ አድርጎ ያቀርባቸዋል። https://www.youtube.com/watch?v=Lk0nRGyAU_s https://www.youtube.com/watch?v=lWEkyH_FLLg

ይህ ሁኔታ በድምሩ ሲታይ የአማራውን ህብረተሰብ በተለይም ደግሞ የጎንደርን ህዝብ ፣የወልቃይት ጠገዴን ነዋሪ ለመብቱ መከበር የሚያካሂደው ትግል እጅግ አስከፊ ለሆነ የዘር ማጥፋት (ብሄር ተኮር ጥቃት ) አደጋ ተጋላጭነቱን ከፍተኛ ያደርገዋል። ይህ የዘር ማጽዳት/ማጥፋት ደግሞ በመንግስት ወታደሮች ብቻ ሳይሆን ህዝብንም ያሳተፈ ለማድረግ ስርአቱ ሰፋሪዎችንም በዚሁ ተግባር ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያዘጋጀውን ወጥመድ በ2008 በወልወቃይት ጠገዴ በተካሄደው “ተሀድሶ” በተሰኘ ዘመቻ ላይ ተግባራዊ ያደረገበት ሁኔታ ከታች የሚታየው መረጃ ያመለክታል።

አገዛዙ በወልቃይት ጠገዴ የፈጸመውን የግፍ መጠን በብአዴን አማካኝነት በጠራውና ጎንደር ላይ በተካሄደው ዝግ ስብሰባ ውስጥ ከተሳታፊዎቹ የተነገረው በከፊል የሚከተለውን ይላል፤

> *" ደርግስ ቢሆን በዚች ሀገር ህጻን ላቀፈች፣ ሴት ይዞ ቤት ለተቀመጠ፣ እንደዚህ አይነት ቦንብ እንደዚህ ያለ አርፒጅ እንዲህ ያለ ብሬን ጥሎ ያውቃልን? "* https://www.youtube.com/watch?v=uKa_steFMYI

## አደጋው ለመፈጸም የተደረጉ ቀደምት ዝግጅቶች

### ሰፈራና ታማኝ የአካባቢ ወታደር ካምፕ ምስረታ

የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊፈጸም ይችላልን የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አንዱ በግልጥ መታየት ያለበት ለዚህ ተግባር የሚደረግ ዝግጅት መኖር አለመኖሩ ነው።

**የዘር ማጽዳት ወይም የዘር ማጥፋት አደጋ ያንዣበበ መሆኑ አንዱ አመላካች ተግባር ገዥው ቡድን የጥቃቱ ኢላማ የሆነውን ህብረተሰብ ላይ ያተኮረ የሀይል ተግባርን ለመጠቀም የሚያስችል በአካባቢው መደበኛ ያልሆን ሰራዊትን ማደራጀትና ማሰማራቱ አንዱ ገጽታ ነው። በአለማችን በታወቁት የዘር ማጥፋትና የዘት ማጽዳት ወንጀሎች በናዚ ጀርመን፣ በቦዝንያ ፣ በሩዋንዳ፣ በዳርፉር ሱዳን፣ በኢንዶኔዥያ፣ በምስራቅ ቲሞር ወዘተ የየሀገሩ መንግስታት መደበኛ ያልሆኑ ሰራዊቶችን መስርተው እንደነበረና እነዚህን ሰራዊቶችም ከፍተኛ እልቂት ለመፈጸም እንደተጠቀሙባቸው ታሪክ ያሳየናል።**

ወልቃይት ጠገዴን በተመለከተ ህወሀት አካባቢውን በቁጥጥሩ ስር ለማዋልና በትግራይ ክልል ስር አስገብቶ ለወታደራዊና ፣ ኢኮኖሚያዊ እቅዱ መሰረት ለማድረግ የወሰነውና መንቀሳቀስም የጀመረው ገና ስልጣን ከመያዙ በፊት ነው።
በተቃዋሚነት ተሰልፎ የትጥቅ ትግል ያካሂድ በነበረበት ጊዜ የወልቃይት ጠገዴን አካባቢ ለወታደራዊ እስትራተጂ በተለይም ወደ ውጭ ለመውጣትና ከውጭ ወደ ትግራይ ማስገባት የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማስገባት በግድ ከሱዳን ጋር የሚያገናኘው በር (መንገድ ) ይፈልግ ነበር።

ቀደም ሲል በወልቃይት ጠገዴ ውስጥ የትጥቅ ትግል ጀምረውና ከህዝቡም ጋር ተዋህደው በመንቀሳቀስ ላይ የነበሩት ኢዴዩ እና ኢህአፓ ደግሞ ከህወሀት ብሄር ተኮር ፖለቲካ መስመር ጋር ተቃራኒ አመለካከት ስለነበራቸው፣ ህወሀት ይህንን አካባቢ ከደርግ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች የፖለቲካ ተቃዋሚዎችም አጽድቶ ለብቻው ለመቆጣጠር እስከ መሳሪያ ፍልሚያ በደረሰ መልኩ በሰፊው ተነቃንቋል።

በሀገር ደረጃ ሰልጣን መቆጣጠር ከቻለበት ( ከ1983 በኢትዮጵያ አቆጣጠር ) በኋላ ደግሞ በሰፈራ እጅግ ሰፊ ቁጥር ያላቸውን በአብዛኛው የህወሀት አባላትና ደራፊ የሆኑ የትግራይ ተወላጆችን ብቻ በአካባቢው በማስፈር የአካባቢውን ህዝብ የብሄር ስብጥር ሙሉ በሙሉ ህወሀት በፈለገው መልክ ለመቀየር ችሏል። በዚህ ሂደት በተለይም በቃፍትያ ሁመራ አካባቢ እንዲሰፍሩ ያደረጋቸው የትግራይ ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ የህወሀት ጠንካራ አባላትንና በከፍተኛ ደረጃ ለድርጅቱ ቅርበት እንዳላቸው በሕወሀት ካድሬዎች የተረጋገጡትን ነበር።

በቃፍትያ ሁመራ በአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1993-94 እስከ 1996 የሰፈሩት በመጀመሪያ ሰፋዋ (SEFAWA ) ተብሎ ከሚጠራው በምስራቅ ሱዳን የሚገኙ የስደተኞች ካምፕ ነዋሪ ከነበሩት ውስጥ በጥንቃቄ በህወሀት ካድሬዎች የተመረጡ 12,000 (አስራ ሁለት ሽህ) የህወሀት አባላትና ታማኞች ብቻ ነበሩ። እነዚህ ተመላሾች የሰፈሩት አዲ አቢ ፣ ማይ ካድራ፣ ራዋያ በተባሉ አካባቢዎች ነው። በሱፋዋ ካምፕ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ስደተኞች በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ 1985 በተከሰተው አስከፊ ረሀብ ምክንያት ከትግራይ በህወሀት አሰተባባሪነት ወደ ሱዳን እንዲሰደዱ የተደረጉ ሲሆኑ ወደ ሲዳን ሲጓዙም ሆነ ሱፋዋ ከደረሱ በኋላ በተከታታይ በህወሀት ፖለቲካ ትምርት ተጠምቀው፣ በሱፋዋ ካምፕም ተደራጅተው ይኖሩ የነበሩ ናቸው።

የሱፋዋ የስድተኛ ካምፕ ከሌሎች የኢትዮጵያ ስደተኞች ካምፖች ጋር ሲወዳደር ሙሉ በሙሉ በህወሀት አባላት የተሞላ እንደነበር ይታወቃል።

ከሱፋዋ ( SEFAWA ) በመቀጠል ለቃፍትያ ሁመራ ሰፈራ የተመረጡት ሌሎች ስደተኞች ደግሞ የመጡት አምራኩባ ከተሰኘው ሌላ በምስራቅ ሱዳን ውስጥ ከሚገኝ ካምፕ ነዋሪዎች ውስጥ የተመረጡ 2225 (ሁለት ሽህ ሁለት መቶ ሀያ አመስት) ሰዎች ናቸው። በመቀጠልም ተዋባና እንጉልጃ ከተሰኙት ካምፖች የተመረጡ 7000 (ሰባት ሽህ) ሰፋሪ ተመላሾች ናቸው። (tewaaba) በተዋባና ( Gwሰji )እንጉልጃ የስደተኛ ካምፖች ከህወሀት በተጨማሪ የኢህአፓና የኢዲዩ (ኢድህ) ደጋፊዎችም በስደተኝነት ይኖሩ ነበር። ሆኖም ግን ወደ ሀገር የመመለስ እንቅስቃሴ ሲካሄድ ይህን ሀላፊነት ተቀብሎ እነማን እንደሚመለሱ የማጣራት ተግባርን ያካሄዱት የማህበር ረድኤት ትግራይ (ማረት፣ ሬሰት ) አባላት ነበሩ። ሬስት ደግሞ የህወሀት እርዳታ ማሰባሰቢያ ክንፍ እንደሆነ ሁሉም የሚያውቀው ነው።

በዚህ ሂደት አሁንም ለሰፈራ የተመረጡት በህወሀት ካድሬዎች ግምገማ የድርጅቱ አባል የሆኑ ወይም ታማኝ ናቸው ተብለው የተመረጡ ብቻ ነበሩ።( kassahun B, 2000, pp 115-124)
ባጠቃላይ በዚህ ሁኔታ ከ1993 እስከ 1996 በነበረው ጊዜ ከ 20 ሽህ በላይ የሆኑ የትግራይ ተወላጆች የሆኑ የህወሀት አባሎችና ቤተሰቦቻቸው ከምስራቅ ሱዳን ከስደት ተመልሰው በቃፍትያ ሁመራ እንዲሰፍሩ ተደርጓል።

ለሰፈራው የተመረጡት ሰዎች ዋና መመዘኛቸው የህወሀት አባላት ወይም ታማኞችና ቤተሰቦቻቸው መሆኑ ሰፈራው ፖለቲካዊና ፣ ወታደራዊ ግቦችን ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ እንደሆነ ያሳያል። ባንድ በኩል ሰፊ ቁጥር ያለው የትግራይ ተወላጆችን ብቻ በማስፈር የአካባቢውን የብሄር ስብጥር ሙሉ በሙሉ በመቀየር የአካባቢውን ወደ ትግራይ መካለል ምክንያት ለመስጠት ሲሆን ሌላው ደግሞ ይህ እርምጃ የሚያስከትለውን ቀጣይ ተቃውሞ በመገንዘብ እስከመጨረሻው አካባቢውን በራሱ የፖለቲካ ታማኞች ቁጥጥር ስር ለማቆየት ቆርጦ የተነሳ ለመሆኑ ግልጽ መረጃ ነው።
በዚህ

**የወልቃይት ጠገዴን የህዝብ ስብጥር የመቀየር እርምጃ (የዘር ማጽዳት ዘመቻ)?**

ስብጥርን በሰፈራ አማካይነት የመቀየር እርምጃ የጥይት ድምጽ ሳይሰማ አካባቢውን የማጽዳት ተግባርን የሚያመለክት ተግባር ነው። በይፋ የተመዘገቡ መረጃዎችንና አሀዞችን ስንመረምር የምናየው የሚከተለውን ሀቅ ይሆናል፡፡

በ1991 የህዝብ ቆጠራ መሰረት የሁመራ አካባቢ (ቃፍትያ ሁመራ ) የህዝብ ብዛት 47 919 ነበር። የ1990 ቁጥር ባይኖረንም ወደኋላ በማስላት ቁጥሩ ስንት አንደነበር መገመት ይቻላል። በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ የሚታየውን የ 2.5% አመታዊ የህዝብ ቁጥር መጨመር ተከትለን ወደሀላ ብንሄድ የምናገኘው 46721 ይሆናል።

በተባበሩት መንግስታት ሪፖርት እንደተገለጠው የህዝቡ ቁጥር በተመለከተ የአማራና የትግራይ ተወላጆች ቁጥር በ1991 እኩል ነበር ይላል UNITED NATIONS EMERGENCIES UNIT FOR ETHIOPIA፤Returnees in Humera፣ PART ONE: Situation report፤(Part 1) http://www.africa.upenn.edu/Hornet/Humera_Repat_1.html

*By Dr. Robert Shank, UN-EUE Field Officer, October, 1994* http://www.africa.upenn.edu/eue_web/Humer_94.htm

ይህን ስሌት ተከትለን በጊዜው የነበረው የአማሮችም ሆነ የትግርኛ ተናጋሪዎች ቁጥር 23 ሽህ በላይ እንደነበረና የትግራይ ተወላጆችም ቁጥር 23፣ ሽህ ነበር ብለን ብንወስድ ፤

ባውሮፓውያን አቆጣጠር በ2007 የተደረገው ቆጠራ ደግሞ በቃፍትያ ሁመራ የነበረው የህዝብ ቁጥር 92167 ሲሆን 86% የትግርኛ ተናጋሪዎች 7% ደግሞ የአማርኛ ተናጋሪዎች እንደሆነ ያሳያል።

ይህ ሁኔታ ያካባቢውን የብሄር ስብጥር እንዴት መቀየር እንደተቻለ በትክልል ያሳያል።

በቅርብ ስንመረምር በ1991 ከነበረው ያካበቢው 46ሽህ ነዋሪ ውስጥ 50% ፣ ማለትም 23ሽህ ያክሉ የአማራ ተወላጆች እንደነበሩ መረጃ ያሳያል። ይህ ቁጥር በያመቱ በ2.5 የህዝብ ቁጥር ይጨምር ነበር ብለን ብንል ከውጭ የተጨመረውን ህዝብ ሳይጨምር፣ በ2007 መሆን የነበረበት ያማሮችም ሆነ የትግራይ ተወላጆች ቁጥር እያንዳንዶ 34፣589 ነው። ሆኖም በ2007 ስታትስቲክ መሰረት በቦታው ከሚኖሩት 92ሽህ ነዋሪዎች ውስጥ የአማራው ቁጥር 7.8% ብቻ ነው ይላል። ይህም ማለት ባጠቃላይ የአማራዎች ቁጥር ከ 7187 (7200) የማይበልጡ ናቸው ማለት ነው።

ጥያቄው ታዲያ 27000 (ሀያ ሰባት ሽህ ) የሚሆኑት አማሮች የት ገቡ የሚለው ነው። ተገደሉ፣ ተሰደዱ ተባረሩ? ወይስ ማንነታቸውን እንዲቀይሩ ተደረጉ? የት ገቡ? ይህ ምላሽ የሚያሰፈልገው እረፍት የሚነሳ ጥያቄ ነው። ብዙዎች ያካባቢው ነዋሪዎችና የመብት ተሟጋቾች፣ ህወሀት ስልጣን እንደያዘ በአማራው ላይ በዘር ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ስለጀመረ የአማራ ተወላጆች መኖሪያቸውን ጥለው እንደተሰደዱና ሌሎች ደግሞ ተቃዋሚ ናችሁ በመባል እንደታሰሩና መዳረሻቸው እንደማይታወቅ ብዙዎች ደግሞ እንደተገደሉ ይናገራሉ።

ባንጻሩ የትግርኛ ተናጋሪዎች ቁጥርስ 86% ማለትም (**79263** ) ከሆነ በተፈጥሮ እድገት መሆን ከሚገባው ቁጥር ከ **34589** በላይ በ **44674** እንዴት አደገ የሚለውን በቅርበት ስንመለከት ምክንያቱ ከአማራው ቁጥር በተጨማሪ ከትግራይ ብሄር ብቻ እየተመረጡ በከፍተኛ ዕቅድ ባካባቢው የተካሄደው ሰፈራ የህዝቡን የብሄር ስብጥር እጅግ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ባጭር ጊዜ እንደቀየረው እናያለን።

ከዚህ ሰፈራ ጋር ተያይዞ ባካባቢው የሚኖረውን የህዝብ ስብጥር ስልታዊ በሆነ መልክ እንዴት መቀየር እንደተቻለ ከዚህ በታች በቀረበው የህዝብ ቁጥር ሰሌት ይታያል።

በዚህ ስሌት ውስጥ የሀገራችን የህዝብ ቁጥር በወቅቱ በያመቱ 2.5% እንደሚያድግ የታወቀ በመሆኑ ይህንኑ ሂሳብ ነው ለስሌቱ የተጠቀምኩት።

በተጨማሪም የተጠቀምኩባቸው የሰፋሪዎች ቁጥሮች በይፋ ከሚገኙ የተባበሩት መንግስታትና ፣ የትግራይ ክልላዊ መንግስት መረጃ አህዞችን ነው። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እኔ ከጠቀስኳቸው በተጨማሪ በተለይም ከአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2003 በኋላ በወልቃይት ጠገዴ በየጊዜው በተከታታይ ሰፋራ እንደሚካሄድና ሁሉም ሰፋሪዎች ደግሞ ከትግራይ ክልል ብቻ የሚመጡ መሆናቸው ይታወቃል። ሆኖም የነዚህን ሰፋሪዎች ብዛትና የሰፈራ ቦታዎች አጠናቅሮ ለማቅረብ ይህ ጽሁፍ እስከተጠናከረበት ጊዜ ስላልተሳካ ፣ ሌሎች ጸሀፊዎች ትኩረት ሰጥተው በቀጣይ ጥናት ክፍተቱን እንደሚሞሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

በአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1993 እስከ 2003 ብቻ በነበረው ጊዜ በወልቃይት ጠገዴ የሰፋሪዎች ቁጥር

**በሁመራ አካባቢ የተካሄደ ሰፈራና የህዝብ ቁጥር መጨመር**

**1993 - 2016**

| የሰፈራው ምንጭ | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 | 1998 | 1999 | 2000 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከሱፋዋ ሱዳን የተመለሱ የመጀመሪያ ሰፋሪዎች | 2200 | | | | | | | |
| ማይ ካድራ May Kadri | 2200 | | | | | | | |
| ራዋይናRawayna | 2600 | | | | | | | |
| አዳባይ Adabay | 7200 | | | | | | | |
| በ1994 ካአምራኩባ ሱዳን የተመለሱ | | 2255 | | | | | | |
| ጠቅላላ የሱዳን ተመላሾች | 12000 | 14፣555 | 14919 | 15፣292 | 15674 | 16066 | 16468 | 16897 |
| ዳንሻ የቀድሞ የህወሀት ተዋጊዎች ሰፈራ | | | 7000 | 7175. | 7354 | 7538. | 7727. | 7920. |
| ዳንሻ የቀድሞ ህወሀት ተዋጊዎች ሰፈራ | | | | | | 22000 | 22550 | 23114 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ ውስጥ የሰፈሩ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | | | | | | | |
| ጠቅላላ ሰፋሪዎች እስከ 2000 | 12000 | 14፣555 | 21929 | 22467 | 23029 | 45604. | 46744 | 47913 |
| **አመተምህረት** | **2001** | **2002** | **2003** | **2004** | **2005** | **2006** | **2007** | **2008** |
| ጠቅላላ የሱዳን ተመላሾች | 17301 | 17734 | 18177 | 18632 | 19097 | 19575 | 20064 | 20566 |
| ዳንሻ የቀድሞ የህወሀት ተዋጊዎች ሰፈራ | 8118 | 8321 | 8529 | 8742 | 8961 | 9185 | 9414 | 9650 |
| ዳንሻ የቀድሞ ህወሀት ተዋጊዎች | 23692 | 24284 | 24891 | 25513 | 26151 | 26805 | 27475 | 28162 |
| በ2003 ሰፈራ ከትግራይ 15 ሽህ ቤተሰብ 75 ሽህ ሰው | | | 75፣000 | 76875 | 78797 | 80767 | 82786 | 84856 |
| ጠቅላላ ሰፋሪዎች እስከ 2008 | 49111 | 50339 | 126597 | 129762 | 133006 | 136331 | 139739 | 143233 |
| **አመተምህረት** | **2009** | **2010** | **2011** | **2012** | **2013** | **2014** | **2015** | **2016** |
| ጠቅላላ የሱዳን ተመላሾች | 21080 | 21607 | 22147 | 22701 | 23268 | 23850 | 24446 | 25507 |
| ዳንሻ የቀድሞ የህወሀት ተዋጊወች ሰፈራ | 9891 | 10138 | 10393 | 10651 | 10918 | 11191 | 11470 | 11757 |
| ዳንሻ የቀድሞ ህወሀት ተዋጊወች ሰፈራ | 28866 | 29588 | 30327 | 31085 | 31863 | 32659 | 33474 | 34312 |
| በ2003 ሰፈራ ከትግራይ 15 ሽህ ቤተሰብ 75 ሽህ ግለሰቦች | 86977 | 89151 | 91380 | 93665 | 96006 | 98406 | 100867 | 103388 |
| ጠቅላላ ሰፋሪዎች እስከ 2016 | 146814 | 150484 | 154246 | 158102 | 162055 | 166106 | 170259 | 174515 |

ይህ ሰፈራ አካባቢውን ህወሀት ወደራሱ ግዛት ( ማለትም ወደትግራይ) ለማጠቃለል የወሰደውን እርምጃ አግባብ ነው ለማሰባል ይረዳዋል። ከ 174 ሽህ በላይ የሚሆኑ እጅግ ታማኝ የሆኑ የድርጅቱና (ህወሀት) የትግራይ ተወላጆችን በቋሚነት እንዲሰፍሩ በማድረግ የወልቃይት ጠገዴን የብሄረሰብ ስብጥር ሙሉ ለሙሉ ቀይሮታል።ይህን ማድረግ ደግሞ የተለያዩ ግቦችን መሰረት ያደረገ ነው።

- ከሰፈራ ወዲህ ባካባቢው የሚታየውን የህዝብ ሰብጥር እንደመረጃ በማቅረብ አካባቢው በዋናነት የትግራይ ተወላጆች የሚኖሩበት ስለሆነ ወደ ትግራይ መቀላቀሉን ትክክል ነበር ለሚለው የህወሀት መከራከሪያ የሚቀርብ መረጃ ይሆናል ፡
- ለም መሬት ከማግኘትም በላይ አካባቢውን ወደትግራይ በማጠቃለል ትግራይ ከሱዳን ጋር በየብስ ለመገናኘት የምትችል ባለ አለም-አቀፍ ድንበርተኛ ክፍለሀገር እንድትሆን ያደርጋታል።
- ታማኝ የድርጅቱ የህወሀትን አባላት በአካባቢው በማሰፈር ሕወሀት ከጎረቤት ሀገሮችም ሆነ ከውጭ በተቃዋሚዎች ሊሰነዘር የሚችልን ተቃውሞ ለመከታተልና መረጃ ለማሰብሰብ እነዚህ ታማኝ ሰፋሪዎች አገልጋይ ሊሆኑ ይችላሉ።

- በመንግስት ላይ በአካባቢው ሊነሳ የሚችልን ማንኛውም ተቃውሞ “ውለታ የተደረገላቸው ሰፋሪዎች” በዋናነት ገና ከጅምሩ እንዲቀጩት ይረዳል። ይህ ደግሞ ባካባቢው በተደጋጋሚ ታይቷል።

ባጠቃላይ የተካሄደው ሰፈራ የአንድን ማህበረሰብ ህዝብ ከመኖሪያው ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ አስለቅቆ በሌላ ያንድ ብሄር ሰዎች ብቻ የተካ ለመሆኑ በማያወላውል ሁኔታ ያሳያል። ይህ ደግሞ በአካባቢው መሰረታዊ የሆነ የዘር ማጽዳት ተግባረዊ የተደረገ ለመሆኑ መረጃ ነው። በቀጣይነትም አካባቢውን ከሌሎች ማህበረሰቦች የጸዳ ለማድረግ ያንዣበበውን ከፍተኛ አደጋም አማላከች ነው።

## የዳንሻ ወታደራዊ ሰፈራ

እጅግ በሚገርም ሁኔታ የህወሀት ኢህአዴግ መንግስት ወልቃይት ጠገዴን በወታደራዊ ሀይል ተቆጣጥሮ ለመውሰድ እንዳቀደና የሀይል ተግባሩ ዝግጅት አንዱ ማሳያ የዳንሻ ወታደራዊ ሰፈራ ፕሮግራም ነው።

የዳንሻ ፕሮጋራም በአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1994_ 1998 ድረስ ከወታደራዊ ተግባር ተቀነሱ የተባሉ 50,000 (ሀምሳ ሽህ ) የህወሀት ታጋዮች እንዲሰፍሩ የተደረገበት ሁኔታ ነው።

አነዚህ ወታደሮች በሙሉ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ በህወሀት ውስጥ እያንዳንዳቸው ቢያንስ የ10 አመት ተሳትፎ ያላቸው ናቸው። ይህ የሚያሳየው በከፍተኛ ደረጃ በድርጅቱ ውስጥ ጥልቅ ትስስር ያላቸው እንደሆኑ ነው። በዚሁ ጊዜ ማለትም እስከ 1998 ባለው ጊዜ ከ200,000 ( ሁለት መቶ ሽህ) በላይ በደርግ ጊዜ በውትድርና የቆዩና 20000 ( ሀያ ሽህ) የኦነግ ሰራዊት አባላት ከውትድርና የተባረሩ እንደሆነ ይታወቃል።

እነዚህ የተባረሩ ቋሚ ወታደሮችና ተዋጊዎች ወደየ ትውልድ ሰፈራቸው እንዲመለሱ ተደረገ እንጂ ልዩ የሰፈራ ቦታ ተፈልጎና ተመቻችቶላቸው ተሰባስበው እንዲሰፍሩ አልተደረገም።

በወታደራዊ አለም ተዋጊ ሀይልን መቀነሰ የተለመደ ተግባር ቢሆንም ህወሀት ያደረገው የቀድሞ ተዋጊ ተቀናሾችን አንድ ላይ ማስፈር ግን በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሰፈራ ፕሮግራሞችም ያልተለመደ አሰራር ነው።

ይህ ሁኔታ የሚያሳየው ህወሀት በርእዮተ አለሙ አጥምቆ ያቆያቸውን የሰራዊት አባላት በቀጣይነት ተደራጅተው እንዲቆዩና በተለመደው ወታደራዊ እዝ ስር ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ምቹና ታማኝ የሆነ አካሎች በተለያየ ቦታ ተሰባሰበው በሚፈለጉ ጊዜ ለወታደራዊ ተግባር ማነቀሳቀስ በሚያስችል ሁኔታ እንዲኖር ማቀዱንና ተግባራዊ ማድረጉን ነው።

የዳንሻ ሰፈራ ወታደሮች ባካባቢው እንዲቆዮ ከሀገር ውስጥና ካለም አቀፍ ማህበረሰቡ ድጋፍና ልዩ ድጎማ ተደርጎላቸዋል። የዳንሻ ወታደራዊ ሰፈራ ጣቢያ የሚገኘው ገና ከመጀመሪያው ወደ ትግራይ በመመደቡ ተቃውሞን ባሰማው የ ወልቃይት ማህበረሰብ መኖሪያ በሆነው በጎንደር ከተማና በሁመራ መሀል ነው።

የዳንሻ ሰፈራና ሌሎችም በሁመራ አካባቢ የተደረጉ ሰፈራዎችን ስንመለከት ህወሀት አካባቢውን በወታደራዊ ሀይል ይዞ ለመቆየት ያለውን እስትራተጂ በግልጥ እናያለን ።

ብዙ የዘር ማጥፋት ወንጀል ጥናቶች እንደሚያሳዩት ደግሞ የዘር ማጥፋት ድንገት የሚከሰት ዱብ እዳ ሳይሆን ሆን ተብሎ በእቅድና በስልት የሚካሄድ መሆኑን ነው። መረጃዎች የሚያሳየው ደግሞ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይ የተደቀነው የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት አደጋ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

**ማህበራዊና ስነልቦናዊ መደላድል**

የዘር ማጥፋት ሊፈጽም እንደሚችል አንዱ አመላካች ሁኔታ ባንድ ህብረተሰብ ውስጥ አንድን የህብረተሰብ ክፍል (ጎሳ፣ ብሄር ወይም የእምነት ተከታይ ) ልዩ ትኩረት በመስጠት በህብረተሰብ ውሰጥ ለሚታይ (ወይም አለ ተብሎ ለሚገመተው) ችግር ተጠያቂ አድርጎ መኮነን፣ ከዚህ አልፎም ጥቃት የተነጣጠረበተ ህዝበ ከሰብእና ውጪ አድርጎ በማቅረብ በዚህ ክፍል

ላይ የሚደረግ ጥቃት ተገቢ እንደሆነና በህግም በሞራልም አስጠያቂ እንዳልሆነ እንዲያውም አግባብ ያለው እርምጃ ተደረጎ እንዲታይ የሚያበረታታ ፣ ተግባር ሲታይ ነው።

የዘር ማጽዳትም ሆነ የዘር ማጥፋት ወንጀል በተካሄደባቸው ህብረተሰበሰቦች ሁሉ የስው ፍጡርን ያክል ክቡር ነገር ላይ የጅምላ ግፍ ለመፈጸም ጥፋቱን ፈጻሚወች የሚያድጉት አንዱና ዋናው የጥቃት ኢላማ የሆነውን ማህበተሰብ አባላት በጅምላ ሰው ቢሆኑም ሰብእና የጎደላቸው አድርጎ ማቅረብ ለህብረተሰብ ችግር፣ ስቃይና መከራ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቶች (ተጠያቂወች) አድርጎ ማሳየት ወይም መወንጀል ዋነናው ተግባር ነው ። ይህ የጥቃት ኢላማ የሆነውን ማህበረሰብ ከሰብእና ውጭ አድርጎ ማሳየት ( ዲ ሂውመናይዚንግ) በዚህ ክፍል ላይ የሚደረግ ጥቃትን ለእምሮ የማይከብድ በማህበረሰብም የማያስወግዝ በሞራልም በህግም ተቀባይነት ያለው ተገቢ እርምጃም አድርጎ ወደ መመልከት ያመራል።
በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም በወልቃይት ጠገዴ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት አደጋ የሚጀምረው አማራውንና ወልቃይቴውን ሰብእና የጎደለው የትግራይ እና የመላ ሀገሪቱ ችግር መሰረት አድርጎ በመፈረጅ ነው።

ህወሀት ገና ከመሰረቱ እንደመነሻ አድርጎ የወሰደው፣ እወክለዋለሁ የሚለውን የትግራይን ህዝብም ይሁን ሌላውን የኢትዮጵያዊያን አሁን ለሚገኙበት ድህነት፣ ሰቆቃ፣ ሓላ ቀርነት፣ የመብት ማጣት ወዘተ ምክንያቱ አማራው ነው የሚል አመለካከት ይዞ ነው። የሚፈለገውን የመብት መጎናጸፍ፣ ለማረጋገጥና ሓላ ቀርነትን ለማጥፋት ደግሞ "የአማራን የበላይነት" ማሰወገድ ብቻ ሳይሆን በርሱ መቃብርም ላይ ሌላ ስርአትን መገንባት ያሰፈልጋል የሚል አመለካከት ነው። ህወሀት በመጀመሪያ ፕሮግራሙ ላይ ያሰፈረው የሚከተለውን ነው።

የህወሀት ባለስልጣኞች ስልጣን ከመያዛቸው በፊትም ሆነ አዲስ አባባ ላይ መንግስተዊ ስልጣን ከያዙ በሓላ የአማራውን ህብረተሰብ የሚያንቋሽሽ ፣ የሀገሪቱ ችግሮች ሁሉ መንስኤ እንደሆነና በጥርጣሬ መታየት ያለበት ማህበረሰብ እነደሆነ በጅምላ በመኮነን ለጥቃል አመቻቻቶታል።

ትምክተኛ የሚል ስያሜ በመስጠትም የአማራው ፍላጎት የሌሎችን መብት ማፈን እንደሆነ በመስበክ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ አማራውን በጅምላ በመጥፎ መልክ እንዲያየው፤ የሚያመቻች የስነ ልቦና ድባብ ፈጥሯል።
የህወሀት ባለስልጣኖች በተደባበቀ ቋንቋ ሳይሆን በግልጽ የአማራን ተወላጅ ምን ያክል ሰብእና ውጭ አድርገው እንደሚመለከቱት አንድ ግልጥ መረጃ ከቀድሞው የአንድነት ፓርቱ አባል ባቀረበ ጽፉፍ ውስጥ በአንድ አዛውንት የአማራ ተወላጅ ላይ የህወሀት ወታደሮች የፈጸሙትን ግፍ ባመላከተ ሁኔታ ባቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ካቀረበው እጅግ አሳዛኝ ምስክርነት የሚከተለውን እንመልከት፡

> " አዛውንቱ በደረሰባቸው ጉዳት ለረጅም ጊዜ ከታመሙ በኋላ ሕይወታቸው አልፏል፡፡ በማግሥቱ ስብሰባ ተጠራንና "በመሥመራችን መሆን ወይም አርፈው መቀመጥ፤ አለባለዚያ ነፍጠኛ-አማራዎችን ምንጣሮ ይቀጥላል፤ እንደ ትላንትናው ሰውዬ ደም እናስተፋለን" በሚል ስብሰባው ይቋጫል፡፡ ከስብሰባው በኋላ በምሳ ላይ "... ግን ግን አዛውንቱ ወንጀለኛ ናቸው ቢባል እንኳ ሳንገል ወይም ሳንደበድብ ጉዳዩን በሕዝብና በተመረጡ ሰላምና መረጋጋት ኮሚቴ ምክር ቤት እንዲታይ ማድረግና ውሳኔውን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም ወይ" ብዬ ጠየኩ አንዱና በጊዜው ትልቁ የፖለቲካ አደራጅ (ባለሥልጣን) የመለሰልኝ ምላሽ "...ደሞ! ለአማራ ይህንን ያህል ትጨነቃለህ እንዴ!" የሚል ነበር፡፡ "እስከ ዛሬ ድረስ ይህ ምላሽ እጅግ እንዳመመኝ ከኔ ጋር ዘልቋል። ውሎ አድሮ ጨዋታውና የጨዋታው ሕግ ለእኔ ግልጽ እየሆነ የመጣ ሲሆን፤ ጉዳዩ ያኔ በረሃ ባሉበት ጊዜ በደርግ ስፍራ ሲተኩ ለማድረግ የወጠኑት ውጥን አካል ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሪዬ እያየለ መጣ፡፡ አዎን ለእኔ እስከገባኝ ከዛ ጊዜ ጀምሮ ኢህአዴግ አማራ የሚባለውን ስም እንደሚጠላ፣ እንደሚፈራ ገባኝ፡፡ ኢህአዴግ የአማራ ተወላጆችን እንደግለሰብም ሆነ እንደ ቡድን ደም እያስተፋቸው፤ የሥራ ቅጥርና የደረጃ ዕድገት እየከለከላቸው፤ የእርሻ ማሳ እየቀማቸው፤ አስተሳሰባቸውን እያመከናቸው፤ ሥነ-ልቦናቸውን እያሸበራቸውና ወኔያቸውን እያኮላሻቸው ይኸው በፍጹም ጥላቻ እያሰቃያቸው ለዛሬ መድረሱን እራሱ ኢሕአዴግ ይክዳል ብዬ አላምንም፡፡ "
> https://sunshineinfotube.blogspot.ca/2017/10/blog-post_49.html

ከላይ የተመለከተው ሁኔታ የሚያሳየው በሰፊው የተካሄደው አማራን ከሰብእና ውጭ አድርጎ የሚያሳይ አመለካከትና ቅስቀሳ በአማራው ላይ የግፍ እርምጃ ለመውሰድ ምንኛ ቀላል እንዳደረገውና ለሚወሰደውም አሳዛኝ እርምጃ (ግድያ) የፈፀመውም ክፍል ምንም ጳጳት እንዳይሰማው እንዳደረገ ነው። በዚህ ሁኔታ ነው አንድን የማህበረሰብ ክፍል ከስብእና ውጭ አድርጎ ማቅረብ ለዘር ማጽዳትና ለዘር ማጥፋት በር ከፋች መደላድል የሚፈጥረው።

ከዚህ በተጨማሪ አሁንም የህወሀት ኢህአዴግ መሪዎች ሲያራግቡት የኖረውን አማራውን ሰብእና እንደሌለው ማመዛዘን እንደማይችል እንስሳ ( አህያ ፣ ..) እንደሚመለከቱት በ2016 የህወሀት ሊቀመንበርና የሀገሪቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በፌስ ቡክ ገጻቸው ያሰፈሩትን የሚከተለውን ማየት ይቻላል።

DR DEBRETSION GEBRE MICHAEL

March 21 ·

> *"በአንድ ሀገር ልማትን ለማምጣት ወሳኙ ሥራ የዜጎችን አእምሮ በማበልፀግ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ነው። መንግሥታችንም ይህንን ለማሳካት ይቻል ዘንድ በርካታ የትምህርት ተቋማትን በማዘጋጀት የሀገሪቱን የተማረ የሰው ኃይል ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ችሏል። ሆኖም በአካዳሚያዊ ዕውቀት ብቻ ሊቀረፉ የማይችሉ እንደ ትምክህተኝነትና ጠባብነት ያሉ አሰሳሰቦችን መቅረፍ የሚቻለው መንግሥት በየጊዜው በሚያካሂዳቸው የተሐድሶ ሥልጠናዎች በመሆኑ፤ ባሁኑ ወቅት ጥልቅ የሆነ የተሐድሶ ፕሮግራም በመካሄድ ላይ ይገኛል። በተለይም ትምክህተኝነትና ጠባብነት በተንሰራፋባቸው በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ሥልጠናው በተጠናከረና በማያቋርጥ ሁኔታ በመሰጠት ላይ ይገኛል።ውጤቱም **ያለጥርጥር እነዚህን በሽታዎች ማስወገድና** የበለጸገች ኢትዮጵያን መገንባት ነው። በመሆኑም ሁላችንም ለተሐድሶ ሥልጠናው መሳካት የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማበርከት አለብን"።*

ይህ ***"ያለጥርጥር እነዚህን በሽታዎች ማስወገድ"***የሚለው አባባል " ህወሀት በጎንደሬው/በወልቃይት ተወላጆች ላይ የሚወስደው እርምጃ እስከምን ሊደርስ እንደሚችል የሚያመላክት ነው። እነዚህን ሁኔታዎች በቅርበት ስንመለከት ህዝቡ በወልቃይት ጠገዴ ጉዳይ ደህንነቱ አደጋ ላይ መሆኑን የሚያሳየው የፖለቲካ ተቃውሞው ከፍተኛ አደገ ሲመጣ ደግሞ ህወሀት ሊወስድ የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን ለመውሰድ የተዘጋጀውን እርምጃ በትክክል የሚያሳይ ነው። መፍትሄው ወደ ማጥፋት ማለትም እልቂት የሚያመራ እንደሆነም በግልጥ ያመላክታል። በአሁኑ ወቅት የህወሀት ሊቀመንበር የሆኑት ዶክተር ደብረጽዮን ይህን ከላይ የተጠቀሰውን የጻፉት የወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ ጋር የተቀሰቀሰው የህዝብ አመጽ ጋር ተያይዞ በመሆኑ ህወሀት ይህን ተቃውሞ ለማፈን ምን ያህል ለመጓዝ ፈቃደኛ መሆኑን ያሳያል።

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ዶክተር ደብረጽዮን የወልቃይትን ንቅናቄ ለማፈን የሚጓዝበትን ጎዳና ባውሮፓ አቆጣጠር በ2016 እንደሚከተለው ያሰረዳሉ Dr Debretsion Gebre Michael June 22 ·

> *በሀገራችን በቅርቡ ተከስተው የነበሩት ብጥብጦችሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ በቊጥጥር ሥር ውለዋል። ይህም ሊሆን የቻለበት ዋነኛ ምክንያት መንግሥት ለሕዝቡ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ በመስጠቱና ነውጥ ፈጣሪዎችን በቊጥጥር ሥር አውሎ ለሕግ በማቅረቡ ነው። ነገር ግን አሁንም ቢሆን በአንዳንድ ክልልሎች ያልረገቡ ነገሮች ይታያሉ። ከነዚህም መካከል ጎንደር ዋነኛ ተጠቃሽ ነው። መንግሥታችን ይህንን አካባቢ ለማረጋጋት ያለውን አቅም በሙሉ አሟጦ በመጠቀም ላይ ቢሆንም ጥረቱ ሙሉ በሙሉ ሊሳካ አልቻለም። በዚህም ሳቢያ በሚቀጥሉት አራት ወራት ውስጥ የጎንደርን አካባቢ ሙሉ በሙሉ ከጦር መሣሪያ ነፃ ለማድረግ እንቅስቃሴ የተጀመረ በመሆኑ በአካባቢው የምትገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ለሰላምና ለመቻቻል ሲባል የጦር መሣሪያዎቻችሁን በየአከባቢያችሁ ለሚገኙ የሚሊሻ አመራሮች በማስረከብ ለሰላም የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ አሳስባለሁ።*

አማራ የሌሎችን ደም የጠጣ (***በሽታዎች*** ): መርዘኛ ነው የሚለው ቅስቀሳ በወይን ሬዲዮ ፣በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በተለያዩ ቋንቋዎች ለ26 አመታት ሳያሰልስ ተካሂዷል፤ አሁንም ይካሄዳል።

በሩዋንዳ ቱትሲዎችን "inyenzi" ወይም በረሮ ( cockroaches) እያሉ ይጠሯቸው እንደነበረ ሁሉ በኢትዮጵያም ይህ አማራውን አውሬ እንደሆነ "አማራ አህያ ነው። አማራ ጅብ ነው። ሆዳም አማራ ፣ አማራ በሽታ ነው አማራ በአውሬ የሚመሰል ጨካኝ ርህራሄ የሌለው ነው" ወዘተ የሚለው ጥላሸት አማራ ሰው ቢሆንም ሰብዕና ግን የጎደለው አድርጎ ከሚያሳየው የረጅም ጊዜ ቅስቃሳ ጋር ሲያያዝ በአማራ ላይ የሚደረግ ጥቃትን እጅግ እንደቀላልና ተገቢ እርምጃ እንዲታይ ፣ የስነልቦና መደላደሉን ሁሉ አመቻችቷል። ድርጊቱን ለሚፈጽመውም ክፍል ጭፍን ጥቃቱ የሞራል ተአቅቦ እንዳይኖር አድርጓል።

የመኢአድ አመራር አባል የሆኑት አቶ ወንድምአገኝ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2013 የተካሄደውን የአማራ ተናጋሪዎች ከየአካባቢው እንዲባረሩ መደረጉን በተመለከተ በሚከተለው የድህረ ገጽ ያለውን ብለው ነበር
https://globalvoices.org/2013/04/11/ethiopia-accused-of-ethnic-cleansing-over-mass-amhara-evictions/

## ማጠቃለያ

ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት፤ በወልቃይት ጠገዴ የአማራው/ ጎንደሬ ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ የዘር ማጽዳት/ የዘር ማጥፋት ሊካሄድበት እንደሚችል ሰፊ መረጃዎች ያሳያሉ። አንዳንዶች በተደጋጋሚ እንደሚያቀርቡት የዘር ማጽዳት ባካባቢው እስካሁንም እየተካሄደ ነው የሚለውን አስተሳሰብ እጅግ ብዙ መረጃወችም ያረጋግጡታል።

ሕወሀት ይህን ለማድረግ በሌሎች ሀገሮች እንደተደረገው ሁሉ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማህበራዊ ምክንያቶች ሲኖሩት ይህን ግፍ ለመፈጸም የሚያስችለው ሰፊ ስነልቦናዊ ስራ እንደሰራና ወታደራዊ ዝግጅቶችም እንዳለው በተጨባጭ ይታያል።
ይህ አደጋ በስልጣን ላይ የሚገኘው ህወሀት መራሹ መንግስት የህዝብ አመጽ እየተጠናከረበት በመጣ ቁጥርም ከዘር ማጽዳቱ አልፎ ወደ ዘር ማጥፋት ሊሸጋገር እንደሚችል አመላካች መረጃወቹ እጅግ ብዙ ናቸው።

ይህንን በተለይ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይ የሚያንጃብብ አደጋ በመገንዘብ ቀጣይ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት አደጋን ለማሰወግድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ ለነገ የማይባል ተግባር ነው።

## አደጋውን ለማስወገድ ምን ይደረግ?

ይህን አደጋ ለማስቆም መደረግ የሚገባቸው የተለያዩ ተግባሮች ሲኖሩ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

- ይህን አደጋ በሰፊው በህዝብ እንዲታወቅ ማድረግ ፣ አለም አቀፉ ህብረተሰቡም ሁኔታውን ይበልጥ እንዲያውቅና የነገሩን አጣዳፊነት እንዲገነዘብ የተጠናከረ እንቅስቃሴ ማድረግ
- በተለይም ደግሞ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመከላከል ከተደራጁ አለም አቀፍ ድርጅቶችና ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጋር በተቀነባበረ መልክ ጥናት እንዲደረግበትና ሰፊ የመከላከያ ስራ እንዲሰራ ማድረግ ይገባል
- ለዚህ ተግባር በዋናነት ተጠያቂ የሆነው ህወሀት መራሹን መንግስት በተለያየ መልክ የሚያግዙ መንግስታትና አለም አቀፍ ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዘር መጥፋት አደጋ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ አጉልቶ በማሳየት ከዚህ አሳፋሪ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ተጽእኖ ማድረግ
- ለአደጋው የተጋለጠውን ህዝብ በማደራጀት፣ የሚሰነዘሩ አደጋዎችን ለተጠቂው ህዝብ በቶሎ ለማሳወቅና ራሱን ለመከላከል እንዲችል የአደጋ መከላከያ ዝግጅቶችን ማድረግ አደጋው ሲፈጸምም በመላ ኢትዮጵያ ያለውን ህዝብ እንዲሁም አላም አቀፍ ህብረተሰቡ ባስቸኳይ እንዲያውቅ የሚያስችል የመረጃ መለዋወጫ እቅድ ማዘጋጀት
- የዚህ አደጋ መሰረት የሆነው የስርአቱ ብሄር ተኮር ፖለቲካ መስመርና የጥላቻ ፖለቲካ ከኢትዮጵያ እንዲወገድና ሁሉም ዜጎች በነጻነትና በእኩልነት በሰላምና በመፈቃቀር ሊኖሩ የሚችሉበትን ስርአት እውን ማድረግ ጥቂቶቹ ናቸው።

## ተጨማሪ መረጃወች

- **የነ ዶክተር ደብረጽዮብ ማስጠንቀቂያ፣ ወታደራዊ ዝመቻ** ፣ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፤
  አደጋውን ለማስወገድ ይቻላልን ከሆነስ እንዴት?
  http://www.wikihow.com/Recognize-the-Warning-Signs-of-Genocide
- **<u>ወልቃይት ትግራይ ወይስ ጎንደር ራስ መንገሻ ምን ይላሉ፤</u>**
  **https://www.youtube.com/watch?v=YNVxvuMR9H8&feature=share**
  **https://sunshineinfotube.blogspot.ca/2017/09/blog-post_27.html**
- **ሕወሀት በአዲስ አባባ ውስጥ** የትግራይን ተወላጅ ወጣቶች ብቻ ሰብስቦ ምን እንደሚል እና ምን ያክል እንደሚጓዝ ባአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2016 ሾልኮ የወጣውን የህወሀት መሪወች ንግግር በሚከተለው ሊንክ ማዳመጥ ይቻላል። **https://www.youtube.com/watch?v=42H8DI9N-ZY&feature=share**
- **የወልቃይት የማንነት ንቅናቄ ና የተሰጠው ምላሽ የ የተሀድሶ ሰብሳባወች በትግራይ፣በወልቃይትና ጠገዴ**
  https://www.youtube.com/watch?v=lWEkyH_FLLg

- “ምርጥ ነገር ለማግኘት መርጥ ወንድሞቻችንን ምርጥ ልጆቻችንን ነው የከፈልነው “ የሚለው በዚህ ቪዲዮ መጀመሪየ የሚሰማው የህወሀት ባለስልጣን ተጋድሏቸውነ መሬት ማስፋፋት ጋር በማያያዝ የደም ካሳ ነው ማለቱ ያንን ይዞ ለመቆየት ሊሄድ የሚችልበትን ጊዞ አመላካች ነው።
- **ዳንሻ አካባቢ የሰፈረው የህወሀት ሰፋሪ በህዝብ መነሳሳቱን ተመልክቶ ያሳዩት ምላሽ** https://www.youtube.com/watch?v=pewQklY1I2Y
- **የወልቃይት ታሪክ https://dagumedia.com/2017/07/30/%E1%8D%96%E1%88%8A%E1%88%B5%E1%89%A0%E1%8B%88%E1%88%8D%E1%89%83%E1%8B%AD%E1%89%B5%E1%8A%AE%E1%88%9A%E1%89%B4%E1%8B%8E%E1%89%BD-%E1%88%8B%E1%8B%AD-%E1%8A%A0%E1%8A%95%E1%8B%B5-%E1%88%9D%E1%88%B5/**